አዋጅ ቁጥር 182/07/2014 ዓ/ም

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የሚሊሺያ ጽህፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም

የወጣ አዋጅ፤

መግቢያ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ህገመንግሥት የተደነገጉ የህዝቦች መብቶችና ጥቅሞች፣ሠላምና ደህንነት መጠበቅና እነዚህን መብቶች በየትኛዉም ኃይል እንዳይጣሱ መከላከል በማስፈለጉ፡ የክልሉን ነዋሪ ፖለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ መብቶችን በኃይልና በአመጽ ለመንጠቅ ከሚቃጡ ኃይሎች በዘላቂነት መከላከልና መጠበቅ በማስፈለጉ፣

በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 3.1 መሠረት የክልሉ ምክር ቤት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

አንቀጽ1

አጭር ርዕስ፣

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የሚሊሺያ ጽህፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 182/07 /2014 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2.

ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. "ክልል" ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ማለት ነዉ።
2. "የሚሊሺያ አባል" ማለት ከግብርና ወይም ከእርሻ ወይም መተዳደሪያ ከሆነ መደበኛ ሥራው ሳይነጠል የመንግሥት ወይም የግል የሆነ፤ለመታጠቅ አግባብ ካለው አካል ፈቃድ ያለው የጦር መሳሪያ የታጠቀና በታጠቀው መሣሪያ ለቀበሌው፣ ለዞኑና ለክልሉ ፀጥታ ሥራ የደመወዝ ክፍያ ሳይኖረዉ አገልግልት የሚሰጥ አባል ነው።
3. "ሚሊሺያ ጽህፈት ቤት" ማለት በየደረጃዉ ያለ የሚሊሺያ ሥራን የማስተባበር አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው።
4. "ጥቅማ ጥቅም" ማለት በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ካለው የኑሮ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ለሚሊሻ አባል የሚሰጥ ድጎማ ነው።
5. "ካሳ" ማለት ለሚሊሻ አባሉ በግዳጅ ወይም በስምሪት ወቅት ለሚደርስ ጉዳት በቁርጥ የሚከፈል የገንዘብ ክፊያ ነው።

6. "ስምሪት" ማለት በየደረጃው በሚገኝ የሚሊሻ ጽህፈት ቤት ለሚሊሻ አባል የአካባቢውንና የሰፈሩን ፀጥታ እንዲያስከብር የሚሰጥ ተልዕኮ ነው፡፡
7. "ጎጥ" ማለት ከቀበሌ ቀጥሎ ያለ ዝቅተኛዉ የአስተዳደር እርከን ነዉ፡፡
8. "ግዳጅ ቦታ" ማለት የፀጥታ ችግር ወይም የተፈጥሮ አደጋ ስጋት ይኖራል ተብሎ ሲገመት ቀድሞ ለመከላከል ወይም ችግሩ ከተከሰተ በኋላ ፀጥታዉን ወይም የተፈጥሮ አደጋዉን በመቆጣጠር ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ የሚሊሻ አባሉ የሚሰማራበት ቦታ ማለት ነዉ፡፡

አንቀጽ 3

የፆታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ዉስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀዉ አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## ክፍል ሁለት

## መቋቋም፣አደረጃጀትና ተጠሪነት፣ዓላማ

አንቀጽ 4

መቋቋም፣

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት የሚሊሺያ ጽህፈት ቤት ከዚህ በኋላ "የሚሊሺያ ጽህፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና የህግ ሰዉነት ያለዉ የመንግስት መስሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል፡፡

አንቀጽ 5.

አደረጃጀት፣

1. የክልል ሚሊሽያ ጽህፈት ቤት ዋና መስሪያ ቤት አሶሳ ከተማ ሆኖ በተዋረድ በዞን፤ በልዩ ወረዳ ፤በወረዳ፤ በከተማ አስተዳደር፤በማዘጋጃ ቤቶች፤ በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋም የሚሊሽያ አደረጃጀት ይኖረዋል፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ አንድ የተመለከተዉ አደረጃጀት እንደተጠበቀ ሆኖ የጎጥ የአስተዳደር እርከን የሚሊሽያ አባላት ይኖሩታል፡፡

አንቀጽ 6.

ተጠሪነት

1. የክልሉ ሚሊሺያ ጽህፈት ቤት ሃላፊ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩና ለመስተዳድር ምክር ቤት ይሆናል፡፡
2. በዞንና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ የሚሊሺያ ጽህፈት ቤቶች ሃላፊዎች በቅደም ተከተል በየደረጃዉ ላሉ የዞንና የወረዳ መስተዳድር ኃላፊና ምክር ቤቶች ይሆናል ፣
3. የቀበሌ ሚሊሺያ ጽህፈት ቤት ተጠሪነቱ ለቀበሌው መስተዳድር ኃላፊና መስተዳድር ይሆናል፣

4. የጎጥ ሚሊሺያ አባል ተጠሪነቱ ለሚኖርበት ቀበሌ ለጎጥ ተጠሪ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 7

ዓላማ

የሚሊሺያ ጽህፈት ቤት የሚከተሉት ዓላማ ይኖሩታል፤-

1. በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህገ መንግስታት የተደነገጉ የህዝቦች መብቶችና ጥቅሞች የመጠበቅ፡፡
2. የክልሉን ህብረተሰብ ሰላምና ደህንነት ከማንኛዉም ጥቃት የመከላከል፡፡

ክፍል ሦስት

የሚሊሺያ ጽህፈት ቤት ሥልጣንና ተግባር፡፡

አንቀጽ 8.

የሚሊሺያ ጽህፈት ቤት የሚከተለት ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፡፡

1. በየእርከኑ የሚገኙ የሚሊሺያ ጽህፈት ቤቶችን ያደራጃል ፣ ያስተባብራል፣ ይመራል፡፡
2. የሚሊሺያን የሰው ኃይል ይመለምላል፣ያሰለጥናል፣ያስታጥቃል፣ትጥቅ ያስፈታል፤ ያደራጃል፣ያሰማራል ያሰናብታል፣አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፡፡
3. የሚሊሺያ አባላትን ብቃት ለማሳደግ የሚያስችል የአቅም ግንባታን ሥራ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን ይሰራል፡፡
4. የጽህፈት ቤቱን አላማ ፈፃሚ የስራ ሂደቶች /ዳይሬክቶሬቶች/፤ ባለሙያዎች እና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፡፡
5. ለሚሊሻ አባላት አስፈላጊ የሆኑ የሎጀስቲክ አቅርቦቶችን ማለትም የደንብ ልብስና እና የመሳሰሉት እንዲሟሉላቸዉ ይሰራል፡፡
6. ከሚመለከተዉ አካል ፈቃድ ሲያገኝ ለሚሊሽያ አባላት የጦር መሳሪያ ግዥ በመፈጸም ያስታጥቃል፡፡
7. የሚሊሻ አባላትን የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፡፡
8. በስራቸዉ የላቀ ዉጤት ያስመዘገቡ የሚሊሻ አባላትን በመለየት ይሸልማል፡፡ አፈፃፀሙ በደንብ ይወሰናል፡፡
9. የሚሊሻ አባሉ ከእርሻ ቦታዉ ወይም በመደበኛነት ከሚሰራበትየስራቦታዉ ሳይነጠል በአካባቢው ፀጥታ የማስከበር እንቅስቃሴዎች ላይ ከክልሉና ለሌሎች የፀጥታ ሃይሎች ጋር የሚሰራበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣
10. ከሁሉም ሴክተር ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡
11. ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

አንቀጽ 9.

ሹመት

1. በርዕሰመስተዳድሩ የሚሾሙ አንድ ጽህፈት ቤት ኃላፊ እና ምክትል ጽህፈት ቤት ኃላፊ ይኖሩታል፡፡

አንቀጽ 10.

የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

1. ጽህፈት ቤቱን ይወክላል፣ የጽህፈት ቤቱን የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፤ይመራል፣

2. የጽህፈት ቤቱን ዕቅድና በጀት እንዲዘጋጅ በማድረግ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል ፣ ሲፈቀድም በሥራ ሊይ ያውላል፣

3. የጽህፈት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ ለሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ ሪፖርት ያቀርባል፣

4. በሚመለከተው አካል የተሰጡ ሌሎች ተግባራትን ይሰራል፡፡

5. የትጥቅና አጠቃላይ የሎጀስቲክ ሂደቶችን ይከታተላል፡፡

አንቀጽ 11.

የጽህፈት ቤቱ ምክትል ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

6. የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፡፡

7. ከኃላፊዉ ተለይተዉ የሚሰጡትን ተግባራትን ያከናዉናል፡፡

8. የጽህፈት ቤቱን ዓላማ ፈፃሚ አደረጃጀቶች ይከታተላል፡፡

9. የሚሊሻ አባሉን ስምሪት በበላይነት ይመራል፡፡

10. ምክትል ጽህፈት ቤት ኃላፊዉ ተጠሪነቱ ለጽህፈት ቤት ኃላፊዉ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 12.

የሚሊሺያ አባል የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

1. ለሚኖርበት አካባቢ ፀጥታ ኃይል ሆኖ ያገለግላል፡፡

2. ወንጀል እንዳይፈፀም ይከላከላል፡፡

3. የሕብረተሰብ ደህንነት ከፖሊስና ከሌሎች የፀጥታ ኃይሎች ጋር በመሆን ያስጠብቃል ይጠብቃል ያስተባብራል፡፡

4. ወንጀል ሲፈጽም ያገኘውን ሰው በህግ አግባብ በቁጥጥር ስር በመዋል ለህግ ያቀርባል፣

5. በመንግሥትና በህዝብ ሠላምና ደህንነት አስጊ ሁኔታ መኖሩን ሲገነዘብ ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

6. አስፈሊጊ ሆኖ ሲገኝ ለሀገር ሠላምና ደህንነት ሲባል ከመከላከያ ሠራዊትና ከሌሎች የፀጥታ ኃይሎች ጋር ይሰራል፡፡

7. የመንግስት ልማትናየመልካም አስተዳደር ተቋማትን በሚሰጠዉ ተልዕኮ መሰረት ክትትልና ጥበቃ ያደርጋል፡፡

## ክፍል አራት

## የሚሊሺያ አባላት መብቶች እና ግዴታዎች፣

### አንቀጽ 13.

### የሚሊሺያ አባላት መብቶች፣

1. ሚሊሻው ከመደበኛ ሥራው ተለይቶ በቀበሌው ዉስጥም ሆነ ከቀበሌው ዉጭበግዳጅ ወይም በስምሪት ላይሲቆይ በቤተሰቡና በመተዳደሪያ ሥራው ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በሚኖርበት ቀበሌ በኩል በአካባቢው በተለመደው አሰራር መሰረት ለቤተሰቡ ጥበቃና እንደ አስፈላጊነቱም ለቤተሰቡ ድጋፍ ይደረግለታል፤ሥራውም ይሸፍንለታል፡፡ አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡
2. የሚሊሻ አባል በግዳጅ ላይ እያለ ጉዳት ቢደርስበት ካሳና ጥቅማጥቅሞች ያገኛል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፣
3. በግዳጅ ላይ እያለ በሞት ለተለየ የሚሊሻ አባል ለቤተሰቡና ተጧሪዎቹ የካሳና የጥቅማጥቅም ክፍያዎች ያገኛሉ፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

### አንቀጽ 14.

### የሚሊሺያ አባል ግዴታዎች፣

1. የሚሊሻ አባል የቀበሌውን፣ የወረዳውን፣ የዞኑንና የክልሉን ፀጥታ የመጠበቅ እና የማስከበር ግዴታ አለበት፡፡
2. ማንኛውም የሚሊሻ አባል የታጠቀውን የጦር መሣሪያና ጥይቶች በአግባቡ መገልገል ይኖርበታል፡፡
3. የሚሊሺያ አባል ከመንግሥትም ሆነ በግል የታጠቀዉን ትጥቅ መሸጥ፣ መለወጥ፣ አሳልፎ መስጠት ፣ ማከራየት እና ሆንብሎ ማበላሸት እና መሰል ድርጊቶችን መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡
4. የአካባቢ ፀጥታ ይጠብቃል፣ ወንጀል እንዳይፈፀምም ይከላከላል፡፡

## ክፍል አምስት

### አንቀጽ 15.

### የሚሊሺያ አባላት ምልመላ፣

1. ኢትዮጵያዊ የሆነ ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፤
2. ጤናማ አዕምሮና አካላዊ ብቃት ያለው፤
3. ማንኛውም ልዩነት ሳይደረግ በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ቀበሌዎች ነዋሪ የሆነ፤

4. በመልካም ሥነ-ምግባር የታነፀ ለመሆኑ የተረጋገጠ የሚሊሺያ አባል ሊሆን ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ አንድ እስከ አራት የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆኖ ስለሚሊሺያ አባላት ምልመላና ስንብት ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

ክፍል ሰድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 16.

ስለ ቅጣት፣

1. ማንኛዉም የሚሊሽያ አባል በአንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ስር የተዘረዘሩ በሚልሻ አባሉ ተጥሰው ሲገኙ በወንጀል ህጉ እና አግባብ ባላቸው ሌሎች ህጎች መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

አንቀጽ 17.

የማንነት መታወቂያ ደብተር፣

የሚሊሺያ አባል የሆነ ሰዉ የአባልነትመታወቂያ ደብተርና የታጠቀዉ መሣሪያም ሕጋዊ ስለመሆኑ የጦር መሳሪያ ፈቃድ መያዝ አለበት፡፡

አንቀጽ 18.

ተፈፃሚነት ስለሌላቸው ሕጎች፣

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፤ ደንብ፤ መመሪያ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 19.

ስለተሻሩ ህጎች፣

የክልሉን አስፈጻሚ አካላት አደረጃጀት፣ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 175/2012አንቀጽ (20) ድንጋጌ ስር ለክልሉ ሰላም ግንባታና ፀጥታ ቢሮ ተሰጥተዉ የነበሩ የክልሉን የሚሊሻ ጽ/ቤት ተግባራት ፤ መብትና ግዴታዎች የያዙ ድንጋጌዎች በሙሉ በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

አንቀጽ 20.

ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፣

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፣
2. የአፈፃፀም መመሪያን የክልሉ ሚሊሺያ ጽህፈት ቤት ሊያወጣ ይችላል፣

አንቀጽ 21.

የመሸጋገሪያ ድንጋጌ ፣

ይህ አዋጅ ከመዉጣቱ በፊት ፍፃሜ ያላገኙ ወይም በሂደት ላይ የነበሩ መብቶች ካሉ በተጀመሩበት አግባብ  ምላሽ ያገኛሉ፡፡

አንቀጽ 22.

አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ ፣

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

መጋቢት 20/07/ 2014 ዓ.ም.

<u>አሶሳ</u>

አሻደሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ኘሬዝዳንት